# የስድስተኛ ክፍል አማርኛ የሞዴል ፈተና መለማመጃ

## ጥያቄ ስድስት

1. የቃላዊ ግጥሞችን ባህርያት የሚያሳየው የቱ ነው?

   ሀ) ቃላዊ በመሆናቸው ቅርጻቸው አጭር ነው

   ለ) ቃላዊ ግጥሞች ለታሪክ ጥናት የመረጃ ምንጮች ናቸው

   ሐ) የበርካታ ሰዎች አሻራ ያረፈባቸው ናቸው

   መ) ሁሉም

2. ኢትዮጵያዊነታችን የሚለው ቃል በምዕላድ ተከፋፍሎ ሲገለጽ፡

   ሀ) ኢትዮጵያዊነት-ኣችን ለ) ኢትዮጵያ-ዊነት-ኣችን

   ሐ) ኢትዮጵያ-ኣዊ-ነት-ኣችን መ) ኢትዮጵያዊ-ነት-ኣችን

3. ከሚከተሉት ቃላት መካከል ሁለተኛ መደብ፣ነጠላ ቁጥር፣ አንስታይ ፆታ የሚያመለክተው ፡

   ሀ) በላሽ ለ) ጠጣህ

   ሐ) ሰበር መ) አሰፋ

4. የአንቀፅን ዋና ሃሳብ የያዘው ዓ/ነገር ምን ይባላል?

   ሀ) መዘርዝር ለ) ሃተታ

   ሐ) ሀይለ ቃል መ) ድርሰት

5. ከሚከተሉት አማራጮች ውስጥ አንዱ የጊዜ ተውሳከ ግስ አይደለም

   ሀ) ዘወትር ለ) አስደሳች

   ሐ) ቀትር መ) ነገ

6. ሰውየው ቁርሱን በልቷል፡፡ ሰውየው እጁን እየታጠበ ነው፡፡ ሰውየው ከሰዓት በኋላ ወደገበያ ይሄዳል፡፡ እነዚህን ሶስት ዓረፍተ ነገሮች የተፃፉበትን ጊዜ በቅደም ተከተል በትክክል የያዘው አማራጭ የትኛው ነው ?

   ሀ) የአሁን ጊዜ፣ የትንቢት ጊዜ፣ የሃላፊ ጊዜ ሐ) የአሁን ጊዜ፣ የሃላፊ ጊዜ፣ የትንቢት ጊዜ

   ለ) የትንቢት ጊዜ፣ የአሁን ጊዜ፣ የሃላፊ ጊዜ መ) የሃላፊ ጊዜ፣ የአሁን ጊዜ፣ የትንቢት ጊዜ

LIVEWORKSHEETS

7. **<u>ልጇት</u>** በሚለው ቃል መድረሻ የገባው ቅጥያ ሙያ ምንን ያመለክታል?

ሀ) እምርነትን ለ) ዖታን

ሐ) ቁጥርን መ) ባለቤትነትን

8. ዘራፊው እጅ ከፍንጅ ሲያዝ **<u>ውሃ ሆነ</u>** የተሰመረበት ሃረግ አውዳዊ ፍቺ፡

ሀ) ደነገጠ ለ) አላበው

ሐ) አመለጠ መ) መሄድ አቃተው

9. ዐመል የሚለው ቃል ዐመለኛ የሆነው የትኛውን ቅጥያ ወስዶ ነው ?

ሀ) ለኛ ለ) ኛ ሐ) ኸኛ መ) አኛ

በእርፍ ቢወቁ በሽመል ቢወቁ፣

በርዬ ካልገባ አርሰበር ምርቁ፡፡

10. ይህ ቃላዊ ግጥም ከየትኛው ቃላዊ ግጥም ውስጥ የመደባል ?

ሀ) በፉከራ ለ) በእርሻ ሐ) በውቂያ መ) በሙሾ

11. ከሚከተሉት ቃላት ውስጥ ውስጠ ግንድ ቅጥያ የታከለበት የትኛው ነው ?

ሀ) ተመቻቸ ለ) ህፃናት ሐ) ከረመ መ) አስመጣ

ከዚህ በታች ለተቀመጡት ቃላት ተቃራኒ የሆኑውን ቃል ምረጡ

12. ቀለጠ

ሀ) ረጋ ለ) ሟሟ ሐ) ከሰረ መ) ሟሸሸ

13. አንጋጠጠች

ሀ) አፈጠጠች ለ) ተማፀነች ሐ) አቀረቀረች መ) አፈረች

14. ህቡዕ

ሀ) ስውር ለ) ግልፅ ሐ) ገሃድ መ) ድብቅ

15. ቅጽበት

ሀ) አጭር ለ) ፍጥነት ሐ) ቆይታ መ) አፍታ

LIVEWORKSHEETS

16. ዋዜማ

ሀ) ቀን ለ) መዳረሻ ሐ) ማግስት መ) ዕለት

ከዚህ በታች ለተቀመጡት ቃላት ተመሳሳይ የሆነውን ቃል ምረጡ

17. መዘላበድ

ሀ) መናገር ለ) ማዛመድ

ሐ) ማበድ መ) መቀበጣጠር

18. ከንቱ

ሀ) የማይጠቅም ለ) ጠቃሚ

ሐ) አስፈላጊ መ) ፅሞና

19. ተፍነከነከ

ሀ) ቦረቀ ለ) ጮቤ ረገጠ

ሐ) ተደሰተ መ) ሁሉም

20. ቤዛ

ሀ) ማስታወሻ ለ) ጥሪት

ሐ) መመኪያ መ) ምሳሌ

21. ወረዛ

ሀ) ረጠበ ለ) ጠፋ

ሐ) ደረቀ መ) ገረረ

22. ወታደሩ ሀገርህን **__አገልግል__** ተባለ፡፡ የተሰመረበት ቃል አውዳዊ ፍቺ፡-

ሀ) ምግብ መያዣ ዕቃ ለ) ከቆዳ የሚዘጋጅ ሐ) እርዳ መ) ሁሉም

23. ከግብረገብነት ይልቅ **__ለንዋይ__** መሯሯጥ የስልጣኔ መገለጫ አይደለም፡፡ የተሰመረበት ቃል ትርጓሜ፡

ሀ) ለእውቀት ለ) ለእድገት ሐ) ለሃብት መ) ስነ ምግባር

LIVEWORKSHEETS

24. .............ቃላት ዓለፍተ ነገሮች እርስበርስ ተቀናጅተውና ተዋህደው እንዲወርቡ የሚያግዙ ቃላትና ሀረጋት ናቸው፡፡

ሀ) ስርዓተ ነጥቦች　　ለ) መስተዋድድ　　ሐ) አያያዥ ቃላት　　መ) መስተፃምር

25. በአማርኛ ቋንቋ መደቦች በስንት ይከፈላሉ ?

ሀ) በአንድ　　ለ) በሶስት　　ሐ) በሁለት　　መ) በአራት

26. ............ ከሌሎች ተማሪዎች በስነ-ምግባር የተመሰከረላችሁ ናችሁ፡፡

ሀ) አንተ　　ለ) እነርሱ　　ሐ) እናንተ　　መ) እኛ

27. **<u>የውሃ ሽታ</u>** ፍካሬያዊ ፍቺ ምን ማለት ነው ?

ሀ) የተበከለ ውሃ　　ለ) ሽታ ያለው ውሃ

ሐ) ደብዛው የጠፋ　　መ) ሽታ የሌለው ውሃ

28. **<u>አጎረሱችው</u>** የሚለው ቃል በየትኛው መደብ ላይ ይገለፃል?

ሀ) 2ኛ መደብ　　ለ) 2ኛ መደብ　　ሐ) 3ኛ መደብ　　መ4ኛ መደብ

29. አባባ ጣሳውን **<u>በጥንቃቄ</u>** ቆረጠው፡፡ የተሰመረበት ቃል የቃል ክፍል ፦

ሀ) ቅፅል　　ለ) ተውላጠ ስም　　ሐ) ተውሳከ ግስ　　መ) ምዕላድ

30. **<u>ከፉኛ</u>** በሚለው ቃል የተመሰረተው ሀረግ ዓይነት ምን ሊሆን ይችላል?

ሀ) ተውሳከ ግሳዊ ሀረግ　　ለ) ቅፅላዊ ሀረግ　　ሐ) ግሳዊ ሀረግ　　መ) ስማዊ ሀረግ

31. **<u>አድሮ ቃሪያ</u>** የሚለው ቃል ትርጉሙ ምን ማለት ነው ?

ሀ) ቶሎ የሚበላሽ ቃሪያ　　ለ) የሚጣል ቃሪይ

ሐ) የማይሻሻል　　መ) ከስተቱ የማይመለስ　　ሠ) ሐ እና መ

LIVEWORKSHEETS

32. ማታ በጊዜ ባለመተኛቱ ጠዋት በጊዜ ሊነሳ አልቻለም፡፡ በዚህ ዓ/ነገር ውስጥ እንደምክኛት ሆኖ የቀረበው ሃሳብ የትኛው ነው?

ሀ) በጠዋት ለመንቃት አለመቻሉ                ለ) ባለመተኛቱ

ሐ) መንቃት አለመቻል                 መ) ማታ በጊዜ ባለመተኛቱ

33. ዛሬ በትምህርትቤታችን ውስጥ **አዳዲስ ሰዎች** ታይተዋል፡፡ በሚለው ዓ/ነገር ውስጥ የተሰመረበትን ቃል ሊተካ የሚችለው ፈሊጥ የቱ ነው ?

ሀ) አይናውጣ        ለ) ስም የለሽ        ሐ) ፀጉረ ልውጥ        መ) እወደድ ባይ

34. **ጉቶ** ለሚለው ቃል እማሪያዊ ፍቺ ሊሆን የሚችለው የቱ ነው?

ሀ) አጭር                ለ) ረጅም

ሐ) እንጨት ተቆርጦ ከስር የሚቀረው አካል                መ) ሀ እና ሐ

35. ከሚከተሉት መካከል ባህሪ አመልካች ቅፅል የሆነው፡-

ሀ) ወፍራም        ለ) ቀጭን        ሐ) ሩህሩህ        መ) ሁሉም

LIVEWORKSHEETS